**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚችሎት**

የሰ/መ/ቁ. 199518
ቀን ፡- ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
ተሾመ ሽፈራው
ሀብታሙ እርቅይሁን
ብርሃኑ መንግስቱ
ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከጆ ሆዕለሞ
2. አቶ አብሬ ክበሞ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ብርሃኑ ሽንቆ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰ/መ/ቁ. 199518
ቀን ፡- ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
ተሾመ ሽፈራው
ሀብታሙ እርቅይሁን
ብርሃኑ መንግስቱ
ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከጆ ሆዕለሞ
2. አቶ አብሬ ክበሞ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ብርሃኑ ሽንቆ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ተከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ የአፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡ ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸው ለተጠሪ የተወሰነው በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከተመዘገበው በላይ የእኛን የይዞታ መሬትና መኖሪያ ቤት ቤትን ጭምር ለተጠሪ አሳልፎ የወሰነ በመሆኑ በተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተመለከተው አግባብ ፍርዱ እንዲፈጸም ጠይቀዋል፡፡ የአፈጻጸም ክርክሩን ሲመራ የነበረው የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤት አመልካቾች እንዲለቁ የተወሰነው መውጪያ መግቢያ ላይ የሠሩትን ቤት ጨምሮ ስለመሆኑ በውሳኔው የተመለከተ በመሆኑና አመልካቾችም ቤቱን ለማንሳት ጊዜ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ቆይተው ቤቱ ያለበት መሬት የእኛ ነው ማለታቸው ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ቤቱ ተነስቶ እንዲፈጽም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በይግባኝ እና በሠበር የተመለከቱት በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ችሎት ውሳኔን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተወሰነው ሁለት ጥማድ መሬት ውጭ መወጪያ መግቢያ በሚል አራት ጥማድ መሬታችን አስረክቡ መባላችን ሆነ ቤት አፍረሱ መባሉ ከፍርዱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ቤት ያፍርሱ መባሉ በውሳኔውና በአፈጻጸም ክሱ መሠረት የተጠየቀ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘቱ አመልካቾች በያዙት ሁለት ጥማድ መሬት ቤት ሰርተው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአፈጻጸም ክርክሩ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውን ፍርድ እና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ነው፡፡ አሁን አከራካሪ ሆኖ የዚህን ችሎት ምላሽ የጠየቀው አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ ተብሎ በአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ በፍርዱ መሠረት እየተፈጸመ ያለ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ በዋናነት ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀረጸው ሠዎች ግጭቶችን ሠላማዊ በሆነ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማስቻል (peaceful resolution of disputes)፣ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ዘዴ እንዲኖርና ፍርድ ቤቶች ክርክርን ፍትሐዊ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዲችሉ ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 መሠረት የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት፡፡ ፍርድ የማይፈጸም ከሆነ የሕግ የበላይነት መገለጫ የሆነውን ዋናውን የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለመወጣት ይሆናል፡፡ ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ ማስፈጸም በመሆኑ ተከራካሪዎች በፍርድ ያረጋገጡትን መብት ሳይፈጸምላቸው ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ እንዳይሆን የመከላከል የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡

በሌላ በኩል የአፈጻጸም ችሎት በመርህ ደረጃ የቀረበን ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በህግ ዳኝነት ለመሥጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ፣ የዳኝነት አካሉ በሕግ አግባብ የተቋቋመ እና የውሳኔው መሠረት የሆነው ነገር ሕልውና ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥና በአጠቃላይ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ የጸና እና የሚያስገድድ መሆኑን መመርመር አለበት፡፡ ዋነኛው የፍርድ መገለጫ የተከራካሪዎችን የፍሬ ነገር ሆነ የሕግ ክርክር ልዩነትን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት መስጠት ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ተግባርም በፍርድ እልባት ያገኘውን መብት ማስፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ ለአፈጻጸም የሚቀርበው ውሳኔ በዚህ ደረጃ ክርክሩን የቋጨና የአፈጻጸም ችሎቱን ወደሙግት ሂደት የማያስገባ መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም አፈጻጸም ችሎት የተከራካሪዎችን መብት በራሱ እየወሰነ ሊያስፈጽም ስለማይችል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ካለኝ 0.306 ሄክታር መሬት በቤተዘመድ ፊት የሠጠሁትን ሁለት ጥማድ የአደራ መሬት ሊያስረክቡኝ ይገባል ሲሆን የሻሾገ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ታህሳስ 06 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ አመልካቾች በአደራ የያዙትን ሁለት ጥማድ

መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፤ ለአፈጻጸም መሠረት የሆነው ውሳኔም ይኸው ነው፡፡ አመልካቾች በውሳኔው መሠረት ሁለት ጥማድ መሬቱን የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤ ይህንን ካልፈጸሙ አፈጻጸም ችሎቱ በውሳኔው በተመለከተው መሠረት ይዞታውን እንዲያስረክቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሁለት ጥማድ መሬቱ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ቢፈጸም ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሠበር አቤቱታው መሠረት ከፍርድ ውጭ ቤትና አራት ጥማድ መሬት ላይ እየተፈጸመ ነው የሚል ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱም የቆርቆሮ ክዳን ቤት አንስተው ፍርዱን እንዲፈጽሙ ማዘዙን ከአፈጻጸም ትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ዋናውን ክስ ያቀረቡ ጊዜ ቤት እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የፍርዱ ይዘት አያሳይም፡፡ ፍርድ ቤቱም በውሳኔ መልክ ያስቀመጠው ሁለት ጥማድ መሬት እንዲለቀቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ገጽ 09 ሁለተኛ አንቀጽ ላይ አመልካቾች ቤት ሰርተው የተጠሪን መውጪያ የከለከሉ ስለመሆኑ መረጋገጡን አስፍሯል፡፡ በፍርድ የሠፈረው ነጥብ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና በፍርዱ ውሳኔ ክፍል ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሚፈጸመው የውሳኔ ክፍል አካል ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤት እንዲፈርስ ለመወሰን በይዞታው ላይ ቤት መሠራቱ ተገልጾ ቤቱ ላይ ግልጽ ዳኝነት ሊጠየቅበት ይገባል፡፡ ቤቱን የሠራው ወገንም ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ቤቱ በማን ይዞታ ላይ ተሰራ? በፈቃድ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም? ሕጋዊ ውጤቱስ ምንድን ነው? የሚሉና ተያያዥ ጭብጦች ተይዘው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡ አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ በዚህ ረገድ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ቤት እንዲፈርስ የተሠጠ ውሳኔ ስለሌለ ቤቱን እንዲያነሱ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ ከፍርዱ ውጭ የሆነና የአመልካቾች መብት የሚጎዳ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አራት ጥማድ መሬት እንድንለቅ በአፈጻጸም እየተገደድን ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ክርክሩ ቤቱ ያለበት ይዞታን የሚጨምር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቤቱ ያለበት ይዞታ በአመልካቾች እጅ ሲቀር ለተጠሪ የሚያስረክቡት ይዞታ መጠን ምን ያህል ይሆናል የሚለው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ላይ የተመለከተው አዋሳኝ እንዲሁም በውሳኔው የተገለጸው ሁለት ጥማድ መሬት ከሚለው ጋር ተጣርቶ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14137 ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20779 መስከረም 29 ቀን 2012 ዓ/ም እና የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ነሀሴ 15 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ቤት እንዲያነሱ/እንዲያፈርሱ በአፈጻጸም ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

3. የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ለአፈጻጸም መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ሁለት ጥማድ ይዞታ አመልካቾች ቤት ከሰሩበት ውጭ ያለውን በማጣራት እንዲያስፈጽም ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. ተጠሪ በይዞታቸው ላይ ቤት ከተሰራ መብታቸውን ክስ አቅርበው ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽም፡፡ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እገድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸው ለተጠሪ የተወሰነው በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከተመዘገበው በላይ የእኛን የይዞታ መሬትና መኖሪያ ቤት ቤትን ጭምር ለተጠሪ አሳልፎ የወሰነ በመሆኑ በተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተመለከተው አግባብ ፍርዱ እንዲፈጸም ጠይቀዋል፡፡ የአፈጻጸም ክርክሩን ሲመራ የነበረው የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤት አመልካቾች እንዲለቁ የተወሰነው መውጪያ መግቢያ ላይ የሠሩትን ቤት ጨምሮ ስለመሆኑ በውሳኔው የተመለከተ በመሆኑና አመልካቾችም ቤቱን ለማንሳት ጊዜ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ቆይተው ቤቱ ያለበት መሬት የእኛ ነው ማለታቸው ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ቤቱ ተነስቶ እንዲፈጽም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በይግባኝ እና በሠበር የተመለከቱት በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ችሎት ውሳኔን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተወሰነው ሁለት ጥማድ መሬት ውጭ መወጪያ መግቢያ በሚል አራት ጥማድ መሬታችን አስረክቡ መባላችን ሆነ ቤት አፍረሱ መባሉ ከፍርዱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ቤት ያፍርሱ መባሉ በውሳኔውና በአፈጻጸም ክሱ መሠረት የተጠየቀ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘቱ አመልካቾች በያዙት ሁለት ጥማድ መሬት ቤት ሰርተው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአፈጻጸም ክርክሩ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውን ፍርድ እና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ነው፡፡ አሁን አከራካሪ ሆኖ የዚህን ችሎት ምላሽ የጠየቀው አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ ተብሎ በአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ በፍርዱ መሠረት እየተፈጸመ ያለ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ በዋናነት ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀረጸው ሠዎች ግጭቶችን ሠላማዊ በሆነ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማስቻል (peaceful resolution of disputes)፣ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ዘዴ እንዲኖርና ፍርድ ቤቶች ክርክርን ፍትሐዊ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዲችሉ ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 መሠረት የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት፡፡ ፍርድ የማይፈጸም ከሆነ የሕግ የበላይነት መገለጫ የሆነውን ዋናውን የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለመወጣት ይሆናል፡፡ ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ ማስፈጸም በመሆኑ ተከራካሪዎች በፍርድ ያረጋገጡትን መብት ሳይፈጸምላቸው ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ እንዳይሆን የመከላከል የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡

በሌላ በኩል የአፈጻጸም ችሎት በመርህ ደረጃ የቀረበን ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በህግ ዳኝነት ለመሥጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ፣ የዳኝነት አካሉ በሕግ አግባብ የተቋቋመ እና የውሳኔው መሠረት የሆነው ነገር ሕልውና ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥና በአጠቃላይ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ የጸና እና የሚያስገድድ መሆኑን መመርመር አለበት፡፡ ዋነኛው የፍርድ መገለጫ የተከራካሪዎችን የፍሬ ነገር ሆነ የሕግ ክርክር ልዩነትን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት መስጠት ነው፡፡ የአፈጻጸም ችሎት ተግባርም በፍርድ እልባት ያገኘውን መብት ማስፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ ለአፈጻጸም የሚቀርበው ውሳኔ በዚህ ደረጃ ክርክሩን የቋጨና የአፈጻጸም ችሎቱን ወደሙግት ሂደት የማያስገባ መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም አፈጻጸም ችሎት የተከራካሪዎችን መብት በራሱ እየወሰነ ሊያስፈጽም ስለማይችል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ካለኝ 0.306 ሄክታር መሬት በቤተዘመድ ፊት የሠጠሁትን ሁለት ጥማድ የአደራ መሬት ሊያስረክቡኝ ይገባል ሲሆን የሻሾገ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ታህሳስ 06 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ አመልካቾች በአደራ የያዙትን ሁለት ጥማድ

መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፤ ለአፈጻጸም መሠረት የሆነው ውሳኔም ይኸው ነው፡፡ አመልካቾች በውሳኔው መሠረት ሁለት ጥማድ መሬቱን የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤ ይህንን ካልፈጸሙ አፈጻጸም ችሎቱ በውሳኔው በተመለከተው መሠረት ይዞታውን እንዲያስረክቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሁለት ጥማድ መሬቱ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ቢፈጸም ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሠበር አቤቱታው መሠረት ከፍርድ ውጭ ቤትና አራት ጥማድ መሬት ላይ እየተፈጸመ ነው የሚል ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱም የቆርቆሮ ክዳን ቤት አንስተው ፍርዱን እንዲፈጽሙ ማዘዙን ከአፈጻጸም ትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ዋናውን ክስ ያቀረቡ ጊዜ ቤት እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የፍርዱ ይዘት አያሳይም፡፡ ፍርድ ቤቱም በውሳኔ መልክ ያስቀመጠው ሁለት ጥማድ መሬት እንዲለቀቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ገጽ 09 ሁለተኛ አንቀጽ ላይ አመልካቾች ቤት ሰርተው የተጠሪን መውጫ የከለከሉ ስለመሆኑ መረጋገጡን አስፍሯል፡፡ በፍርድ የሠፈረው ነጥብ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና በፍርዱ ውሳኔ ክፍል ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሚፈጸመው የውሳኔ ክፍል አካል ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤት እንዲፈርስ ለመወሰን በይዞታው ላይ ቤት መሠራቱ ተገልጾ ቤቱ ላይ ግልጽ ዳኝነት ሊጠየቅበት ይገባል፡፡ ቤቱን የሠራው ወገንም ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ቤቱ በማን ይዞታ ላይ ተሰራ? በፈቃድ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም? ሕጋዊ ውጤቱስ ምንድን ነው? የሚሉና ተያያዥ ጭብጦች ተይዘው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡ አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ በዚህ ረገድ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ቤት እንዲፈርስ የተሠጠ ውሳኔ ስለሌለ ቤቱን እንዲያነሱ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ ከፍርዱ ውጭ የሆነና የአመልካቾች መብት የሚጎዳ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አራት ጥማድ መሬት እንድንለቅ በአፈጻጸም እየተገደድን ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ክርክሩ ቤቱ ያለበት ይዞታን የሚጨምር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቤቱ ያለበት ይዞታ በአመልካቾች እጅ ሲቀር ለተጠሪ የሚያስረክቡት ይዞታ መጠን ምን ያህል ይሆናል የሚለው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ላይ የተመለከተው አዋሳኝ እንዲሁም በውሳኔው የተገለጸው ሁለት ጥማድ መሬት ከሚለው ጋር ተጣርቶ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14137 ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20779 መስከረም 29 ቀን 2012 ዓ/ም እና የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ነሀሴ 15 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ቤት እንዲያነሱ/እንዲያፈርሱ በአፈጻጸም ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

3. የሻሾን ወረዳ ፍርድ ቤት ለአፈጻጸም መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ሁለት ጥማድ ይዞታ አመልካቾች ቤት ከሰሩበት ውጭ ያለውን በማጣራት እንዲያስፈጽም ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. ተጠሪ በይዞታቸው ላይ ቤት ከተሰራ መብታቸውን ክስ አቅርበው ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሻሾን ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽም፡፡ይጻፍ
- ❖ አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እገድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ